Bundesamt
für Migration
und Flüchtlinge

# እስቲ ልናማክራችሁ

የምክር አገልግሎት ለስደተኞች

AMHARISCH



Integration

JUGEND MIGRATIONS DIENSTE

MBE
Migrationsberatung
für erwachsene Zuwanderer



# በነጻ ለግለሰብ የሚሰጡ የስደተኞች የምክር አገልግሎቶች ተጠቀሙበት ፡

## የምክር አገልግሎት ለአዋቂዎች ስደተኞት (MBE) እና የምክር አገልግሎት ለወጣቶች ስደተኞች (JMD)

### የግለሰብ ምክር ጠቀሜታዎች

መጀመርያ ላይ በጀርመን ብዙ ነገሮች እንግዳ እና ያልተለመዱ ሊሆንብዎት ይችላሉ ። በጀርመን አገር ለብዙ ግዜ ብትቀመጡም ገና መልስ የምትፈልጉላቸው ጥያቄዎች ሊኖሩ ይችላሉ ።

ለእናንተ ተብሎ ከመጀመርያ የተዘጋጀ የግለሰብ ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ይሄን ለማድረግ ይረዳዎታል። ይሄን ለሁሉም በዕለተዕለት ሕይወት ውስጥ ያሉሁ ኔታዎችሁ ተጨባጭ ድጋፍ ይሰጣል። በዚህ መንገድ ፣ ጉዳዮቻችሁን እንዴት በራሳችሁ እጅ እንደምታስገቡ እና በነጻነት ውሳኔ መስጠት እንደምትችሉ ትማራላችሁ።



## የምክር አገልግሎቶች ለአዋቂዎች እና ለወጣት ስደተኞች

የአዋቂዎች የፍልሰት የምክር አገልግሎት ዕድሚያቸው ከ 27 ዓመት በላይ ለሆኑ ጎልማሶች ስደተኞች ምክር ይሰጣል።

የወጣቶች የፍልሰት የምክር አገልግሎት ዕድሚያቸው ከ 12 እስከ 27 ዓመት ለሆኑ እና የተላያየ የጀርባ ታሪክ ላላቸው ወጣቶች ስደተኞች ምክር ይሰጣል።

በመርህ ደረጃ ፡ ሁለቱን የአዋቂዎች እና የወጣቶች የፍልሰት የምክር አገልግሎቶች ማነጋገር ትችላላችሁ። የመጀመርያ ቃለ መጠይቅ ካደረጋችሁ በኋላ የሚቀጥለው አሰራር የምክር አገልግሎቶች በሚያደርጉት ቅንጅት ይወሰናል። በዚህ የእርስዎ የግል ሁኔታ እና የቤተሰብዎ አባላት ሁኔታዎች በግምት ይከተታሉ።

## የተሻሉ ዕድሎች በግል የምክር አገልግሎቶች

የምክር ተቋማት ሰራተኞች እንዲሁ የትውልድ አገራችሁን ቋንቋ ይረዳሉ። በተጨማሪም የናንተ ማህበራዊ ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ የአስተሳሰብ መንገዶች እና አመለካከቶች ያውቃሉ። በጀርመን ለመጀመርያ እርምጃችሁ መመሪያዎች የሚሆኑ እቅዶች ከእናንተ ጋር በመሆን ያወጣሉ። ምክሮቹ በእናንተየግል ችሎታዎች እና እውቀት ላይ ያተኩራሉ። በጀርመን በቀላሉ ለመኖር ምስ ዓይነት የድጋፍ አገልግሎቶች እንዳሉም ታገኛላችሁ።

በምክር ወቅት ሁሉንም የዕለትተዕለት ሕይወት ርዕሶች መፍታት ይችላሉ። ለምሳሌ፣

- ስለ መኖሪያችሁ የሚመለከቱ የህግ ጥያቄዎች
- የጀርመን ቋንቋ መማር (ለምሳሌ በውህደት ኮርስ ውስጥ መሳተፍ)
- የትምህርት ቤት ትምህርት፣ የሙያ ሥልጠና (ለምሳሌ የትምህርት ቤት ሥራዎች፣ የሥልጠና መንገዶች፣ ለሙያ ብቃቶች ዕውቅና መስጠት)
- ሙያዊ እንቅስቃሴ (ለምሳሌ ፣ የሥራ ማመልከቻ ስልጠና፣ ሥራፍለጋ
- ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ (ለምሳሌ፣ ገቢ፣ ብድር፣ ዕዳዎች)
- መኖሪያ ቤት (ለምሳሌ፣ ቤት ማግኘት፣ ክፍያ የቤት እንዴት እንደሚደረግ)
- ጤና (ለምሳሌ ፣ የጤና መድህን፣ ህክምናዊ እንክብካቤ)
- የግል የጤና ሁኔታ (ለምሳሌ፣ የጤና ችግሮች)
- ጋብቻ፣ ቤተሰብ እና ትምህርት (ለምሳሌ ፣ እርግዝና)
- ተንቀሳቃሽነት እና መጓጓዣ (ለምሳሌ ፣ የማሽከርከርያ ፈቃድ፣ የህዝብ ማመላለሻ)
- መዝናኛ፣ ስፖርት እና የእረፍት ግዜ (ለምሳሌ ክፍት ቅናሾች፣ የክለቦች አባልነት)
- የዕለትተዕለት እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ፣ ግብይት፣ ከባለስልጣናት ጋር መገናኘት)

## የወጣቶች ፍልሰት አገልግሎቶች ልዩ ስጦታዎች ለየፍልሰት የጀርባ ታሪክ ያላቸው ወጣቶች

ለወጣቶች ፡ ለመጀመርያ ግዜ በባዕድ አገር ኣስደሳች ነው ፣ ግን ደግሞ ኣስጨናቂም ጭምር ነው። በትምህርት ቤት ፣ በስልጠና ቦታ ፣ በስራ ቦታ እና እንዲሁም አዲስ ትውውቅ ለመፍጣር ያሉ ጫናዎችን ማቋቋም አለባችሁ። የወጣቶች ፍልሰት የምክር አገልግሎቶች በእናንተ ላይ ያተኮሩ የተወሰኑ ሽግራችሁ እና ጥያቄያችሁ የሚመልሱ የግል ምክር ፣ የተጠናከረ ድጋፍና እና የቡድን አገልግሎቶች ይሰጣል።

በሚቀጥሉት ርዕሶች ላይ ስጦታዎች ታገኛላችሁ ፣ ከብዙዎቹ በጥቂት፣

- ስለ ትምህርትቤት እና የሥልጠና ስርዓት
- የግል ስልጠና እና የሙያ እቅድ ማውጣት (ከአከባቢው የሥራ ስምሪት ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር)
- በሁሉም ማህበራዊ ፡ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ህይወቶም ለመሳተፍ
- ከአዳዲስ መገናኛ በተለይ የጀርመን ቋንቋ መማርያ ፕሮግራሞች ጋር ግኑኝነት ለማድረግ




## የኢንተርነት መስመር ላይ ምክር

ከግል ምክር በተጨማሪ ሁለቱም የምክር አገልግሎቶች በኢንተርነት መስመር ላይ ምክር የመስጠት ዕድል አመቻችቶላቹሃል። "mbeon" የኢንተርነት መስመር የምክር ኣገልግሎት እና jmd4you የምክር በር ጥያቄያችሁን በኣጭር ጽሁፍ ለመላክ ይረዱዎታል!

በ mbeon በኩል ፡ የግል መመሪያ እና ድጋፍ በውይይት መልክ ልትቀበሉና እና ጥያቂያችሁ በሰዓቱ ኣጠገብ ባለው መላክ ትችላላችሁ። ምክር በ mbeon አፕሊኬሽን በበርካታ ቋንቋዎች ይዘጋጃል። ስለዚህ በ mbeon ለናንተ ተብለው የተዘጋጁ በቋንቋችሁ የሚናገሩ አማካሪዎች ታገኛላችሁ።

- *www.mbeon.de*

ዕድሚያቸው እስከ 27 ዓመት ለሆኑ ወጣት ስደተኞች በኢንተርነት መስመር ላይ ምክር የማግኘት ዕድል አላቸው። ጥያቄዎች በይፋ በውይይት መተግበሪያው ሳጥን ፡ ወይም በግል ማቅረብ ይችላሉ። መልሶቹ የዳበረ ልምድ ባላቸው የ JMD ነው የሚሰጠው።

- ጀርመን *www.jmd4you.de*, እንዲሁም በ
- እንግሊዝ *www.your-way-in-germany.org*
- ሩስያ *www.putjwgermaniju.org*
- ቱርክ *www.almanyayolu.org*
- ዓረብ *www.bousaletuk-fi-almanya.org*
- ኣልባንያ *www.udherrefyesi-gjermani.org*

ሁልግዜ የቤተሰብ አባላት ፣ ጓደኞችን ፣ የስራ ባልደረቦች ፣ ከእናንተ ጋር አብረው ለሚኖሩ፣ ከእናንተ ጋር ላሉ የስፖርት ክለብ አባላት የተወሰኑ የምክር ኣገልግሎቶች ጠይቁ።

የበለጠ ይፈልጉ እና ከነጻ የምክር ኣገልግሎቶች ያትርፉ!

## ስለ ምክር አገልግሎት ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት ትችላላችሁ?

በተወሰኑ የምክር አገልግሎቶች መረጃ ለማግኘት እዚህ ቀጥለው በተዘረዘሩት በክልላችሁ በሚገኙ ፡ በተለይ ከ

- የማዘጋጃቤት፣ የከተማ ወይም የወረዳአ ስተዳደሮች (Gemeinde-, Stadt- oder Kreisverwaltungen)
- በማህበራት ከለላ የተሰማሩ የበጎ ኣድራጎት ድርጅቶች (በጎ ኣድራጎት የሰራተኞች ደህንነት (Arbeiterwohlfahrt)፣ ካሪታስ ጀርመን የእርዳታ ማህበር (Deutscher Caritasverband)፣ ዲያኮኒ ጀርመን - ወንጌላዊ የበጎ ኣድራጎት ድርጅት የሃልዮት ስራ እና ልማት (Diakonie Deutschland-Evangelisches Werk für Diakonie und Entwicklung) ፣ ጀርመን ቀይ መስቀል (Deutsches Rotes Kreuz)፣ የጀርመን የእኩልነት በጎ ኣድራጎት ማህበር (Deutscher Paritätischer Wohlfahrtsverband)፣ የ ኣይሁዳውያን በጎ ኣድራጎት ማእከላዊ ጽህፈት ቤት በጀርመን (Zentralwohlfahrtsstelle der Juden in Deutschland))
- የተባረሩት የሚያደራጅ እና ታሪካቸው የሚዘግብ ፌደሬሽን (Bund der Vertriebenen)
- የዓለም አቀፍ ፌደረሽን (Internationaler Bund)
- የወጣት ማህበራዊ ሥራ አቅራቢዎች (Träger der Jugendsozialarbeit)
- የውህደት ትምህርቶች አቅራቢዎች (Träger der Intergrationskurse)

## በኢንተርነት መረጃ ልናገኝባቸው የሚችሉ ኣድራሻዎች ፡

- *www.bamf.de/DE/Themen/Integration/ZugewanderteTeilnehmende/BeratungErwachsene/beratung-erwachsene-node.html*
- *www.mbeon.de* እና
- *www.facebook.com/mbeon.chat*
- *www.jugendmigrationsdienste.de*

## ህትመት

**አሳታሚ ፣**
Bundesamt für Migration und Flüchtlinge
90461 Nürnberg

**እዋን**:
10/2020

**ማተሚያ ቤት**:
Silber Druck oHG, Lohfelden

**ዲዛይን**:
MediaCompany – Agentur für Kommunikatikon GmbH

**ምስል ክሬዲት**:
istock / sturti, istock / lisegagne, istock / SDI Productions,
BAMF / Bildkraftwerk / Thomas Geiger

**የትእዛዝ ኣማራጮ ፣**
Publikationsstelle des Bundesamtes für Migration und Flüchtlinge
www.bamf.de / publikationen

እንዲሁም ይህንን ህትመት እንደ ተደራሽ (ማገጃ-ነፃ) የፒዲኤፍ ሰነድ ማውረድ ይችላሉ ከ: www.bamf.de / publikationen

ይህ ህትመት በፌደራል የፍልሰት እና ስደት ጽህፈት ቤት እንደ ህዝባዊ ግኑኝነቶች ኣካል የታተመ ነው። ይሄን ህትመት በነጻ የሚሰት እና ለሽያጭ የታሰበ ኣይደለም።

ይጎብኙን በ ፣
www.facebook.com/bamf.socialmedia
@BAMF_Dialog
www.bamf.de

Other Language
www.bamf.de/publikationen